| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ፨ |
| ርእስ ፤ | "ኧረ ፡ መልካም ፡ ዐዲስ ፡ ዓመት!" |
| ደራሲ ፤ | ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ፨ |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ፨ |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ፨ |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ፨

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

# ኧረ ፡ መልካም ፡ ዐዲስ ፡ ዓመት!

---

እንኳን ፡ ከዘመነ ፡ ሉቃስ ፡ ወደ ፡ ዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ በሰላም ፡ አሸጋገራችኹ! ፡ እያልን ፡ ፳፻፲፪ ፡ ዓ.ም. ፡ የሰላም ፤ የፍቅር ፤ የነጻነትና ፡ ያንድነት ፡ ዓመት ፡ እንዲኾንልን ፡ ከልብ ፡ እንመኛለን ፨

በ፳፻፲ ፡ ዓ.ም. ፡ እተልእኮው ፡ ጫፍ ፡ የደረሰው ፡ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ *"ለሥር-ነቀል ፡ ለውጥ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ"* ፡ ሲል ፡ የለውጥ ፡ ፍላጎቱን ፡ አሰምቶ ፥ እስረኞችን ፡ በከፊል ፡ ፈታ ፤ ሕዝብም ፡ *"ዕሠዬው!"* ፡ አለ ፨ *"ተወዳዳሪ"* ፡ ያላቸውን ፡ የስያሳ ፡ ቡድኖችም ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ገብተው ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ እንዲሳተፉ ፡ *"ፈቀደላቸው"* ፤ ሕዝብም ፡ *"በጀ!"* ፡ አለ ፨ ቀጥሎ ፥ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ሹመኞች ፡ *"ሕዝብ ፡ ይቅር ፡ ብሎናል"* ፡ አሉ ፤ ሕዝብ ፡ ዝም ፡ አለ ፤ ምን ፡ ይበል ፡ ... ፥ ከጨቈና ፡ ገና ፡ አልወጣ! ቀጥሎ ፡ *"እኔ ፡ አሸጋግራችኋለኹ"* ፡ አለ ፤ አኹንም ፡ ሕዝብ ፡ ዝም ፡ አለ ፤ ምን ፡ ይበል ፡ ... ፥ *"ውረድ!"* ፡ የሚልበትን ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉን ፡ ገና ፡ አልሠራ!

፳፻፲፩ ፡ ዓ.ም. ፡ *"ላም ፡ አለኝ ፡ በሰማይ ፥ ወተቷን ፡ እማላይ"* ፥ በከንቱ ፡ ተስፋ ፡ ዐለፈ ፨ *"ግንቡም"* ፡ ሳይፈርስ ፡ ተጠናክሮ ፥ *"ድልድዩም"* ፡ ሳይሠራ ፡ ተጭበርብሮ ፥ ቃል ፡ የተገባው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ግንቦት ፡ ጤዛ ፡ ሳይነጋ ፡ ተኖ ፡ ጠፋ ፨ በምትኩ ፥ በሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ንጹሓን ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በተደራጁ ፡ የጥፋት ፡ ኀይሎች ፡ ተገደሉ ፤ በሚልዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ከቦታቸው ፡ ተፈናቀሉ ፨

በ፳፻፲፩ ፡ ዓ.ም. ፥ *"ደባሉ ፡ መንግሥት"* ፡ ዐቅሙን ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ለክልል ፡ *"መንግሥታት"* ፡ ወዶ ፡ ፈቅዶ ፡ እያስረከበ ፥ ከቍጥርጥሩ ፡ ውጭ ፡ ኾነው ፥ ቢያስፈልጋቸው ፡ *"አንታዘዝም"* ፡ እሚሉበት ፡ የዛሬ ፡ ደረጃቸው ፡ አደረሳቸው ፤ ከዚህም ፡ ዐልፈው ፡ *"የዘር ፡ ማጽዳት"* ፡ ዘመቻቸውን ፡ አጠናክረው ፡ ቀጠሉ ፨ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተቃጠሉ ፤ ካህናት ፡ ታረዱ ፤ መሰናክል ፡ ይኾናሉ ፡ የተባሉ ፡ የ*"ክልል"* ፡ አመራር ፡ አባሎች ፡ በቅድሚያ ፡ ተወገዱ ፤ የባላደራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባላትን ፡ ጨምሮ ፥ የሰብኣዊ ፡ መብት ፡ ተሟጋቾች ፡ ታፍሰው ፡ ታሰሩ ፤ አረንጓዴ ፤ ብጫ ፤ ቀይ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማችን ፡ በ*"ሕገ ፡ ወጦች"* ፡ *"ሕገ ፡ ወጥ"* ፡ ተባለች ፤ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተደፈረች ፨

መጪው ፡ ዘመን ፡ ሀገሪቱን ፡ ለከፋ ፡ አደጋ ፡ የሚዳርግ ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፡ ጠቅላላው ፡ ኹኔታ ፡ ምልክቶችን ፡ እንሆ ፡ አሳይቷል ፨ መንግሥት-አልቦው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉን ፡ በፍጥነት ፡ ደርጅቶ ፡ እግዚእናውን ፡ ከማስከበርና ፡ ሀገሩን ፡ ከመታደግ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ማማረጫ ፡ ስለማይኖረው ፥ እንሆ ፡ ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ ባገር ፡ ፍቅር ፡ ላስተላለፈለት ፡ ጥሪ ፡ አቤት ፡ ይበለው ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፨
ሥልጡንሕዝብና ፨
www.slttunhzb.net


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ፨